# ኢትዮጵያ እየፈረሰች ትግራይ ልትቆም?
# አቶ አረጋዊ በርሄ በአገር አሉ? የት ናቸው?

(ከግርማ ታፈሰ)

ህወሓት ብሎ ራሱን የሚጠራው ይህ ድርጅት ገና ትግል ሲጀምር በ1967 ዓ.ም(ኢ.ት.አ.) የቀረጸው ህልሙ ትግራይ ትግርኝ "ታላቂቱን ትግራይ" መመስረት ነው። ዛሬ ይሄንን ህልሙን በሥራ ላይ ለማዋል ደፋ ቀና የሚለው ወያኔ/ህወሓት ገና ያኔ በጨርቃነቱ ለትግራይ ህዝብ ነጻነት ነው የምታገለው እያለ የትግራይ ትግርኝ ሕልሙን የቀረጸበት አይታው ኢትዮጵያን አፍርሶ በፈረሰችው ኢትዮጵያ ላይ ትግራይ ትግርኝ ወይም "ታላቋን ትግራይ" ለመትከል ነበር። ዋና ዓላማው ይሄ ነው። ይህ ድርጅት ሲመሠረት ጀምሮ ይህንን ህልሙን ሥራ ላይ ለማዋል በኢትዮጵያዊነት ላይ ጦር ሰብቆ፣ በኢትዮጵያዊያን ሬሳ ላይ ተረማምዶ የሚያቆማትን ትግራይ ትግርኝ፣ "ታላቋ ትግራይ" የምስራቅ አፍሪካ ዋልታና ምሰሶ ለማድረግም ነበር። ለነገሩማ ይህ ያበደ ድርጅት እንደ ቀድሞው ምኞቱና ፍላጎቱ ተሳክቶለት ቢሆን ኖሮ የዛሬዋን ኤርትራ ከትግራይ ጋር በማድረግ፣ የትግራይ ትግርኝን መንግሥት አቋቁሞ የትግራይ ትግርኝ ባለቤት ለመሆን ነበር የህወሓት/ወያኔ ምኞት። "እባብን የልቡን ክፋት አይቶ እግር ነሳው" ሆነና ነገሩ ያ ህልም ባሰበውና በፈለገው መንገድ አልሄድ ብሎት ይኸውና ተንገራግጮ ቆሟል። ይህ እምነት የተሓህት/ህወሓት ወያኔ መሥራቾችን በሙሉ ያማለለና ለዚህ ለቃዡበት ህልማቸው ደግሞ ገና ዳዴ ብለው ሲጀምሩ ብዙ ኢትዮጵያዊያንን በትግራይ ትግርኝ ወያኔያዊ ሰይፍ አንገታቸውን እየቀሉ፣ በኢትዮጵያዊነት ስም የተደራጁ ድርጅቶችን (እነ ኢዲዩና ኢሕአፓን ያስታውሷል) ወደ ትግራይ ምድር ብቅ እንዳይሉ በሰይፋቸው እየመቱና/እያረዱ ከትግራይ መሬት ያባረሩ ናቸው።

ይህ ጠባብ ድርጅት ዛሬም በውስጡ የቀጠሉትና በተለያየ ምክንያትም ከዚህ ጠባብ ድርጅት የወጡት (በሙሉ ማለት ይችላል) ከ"ታላቋ ትግራይ" አንጻር የተነጣጠሉ እየመሰሉ ግን አንድ ሆነው በመጓዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ሕዝብ፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ ሀገር አሁን ለደረሰችበት ጣጣና ለምትገኝበት ጣር ሁሉ 33 ዓመት ሙሉ ተግተው የተጓዙበት የጋራ ሂደት ነው። ይህንን ህልም አቶ አረጋዊ በርሄም ይጋሩታል፤ እርግጥ ነው ይህንን የቅዠት ህልም አሁን አቶ አረጋዊ በግልጽ በአደባባይ ሊያወጡና ሊናገሩ በማያስችላቸው ሁኔታ ሰለገቡና ሰለወደቁ እንጅ፣ የህወሓት/ወያኔ መስራችና ሊቀ መንበር ሆነው ባገለገሉበት ወቅት እሳቸው ባሉበትና በተቀመጡበት የተቀረጸና የተበጀ የህወሓት(የቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ) ህልምና ካርታ ነው። ይህ ኢትዮጵያን የሚያፈራርሰው ካርታ ሲሰራም አቶ አረጋዊ በርሄ በወቅቱና በቦታው የነበሩ የመጀመርያው የድርጅቱ ዋና ሰው ናቸው። እንደ እዉነቱ ከሆነ የዛሬው የቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ሊቀ መንበር አቶ መለስ ዜናዊ አሁን የያዙትን የቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ሊቀ መንበርነትን እንኳን የወሰዱት ከአቶ አረጋዊ በርሄ እጅ መሆኑን የድርጅታቸው ታሪክ ዘግቦት ይገኛል።

ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ከምሥረታው ጀምሮ ኢትዮጵያዊነትን ያስቀደሙና በኢትዮጵያዊነት የሚኮሩ ዜጎችን በሙሉ ትግራይ ውስጥ ሁሉ ሳይቀር እያደነ አንድ በአንድ ካጠፋ በኋላ በራሱ በድርጅቱ ውስጥም በአንድ በትግራይ የጠባብነት ዓላማ ሥር የተሰለፉትም ቢሆኑ በሥልጣን ግብግብ ሳቢያ እርስ በርሳቸው ተጋድለዋል ብዙ ደም ተፋሰዋል። አሁን ህወሓት/ወያኔ የተባለው ድርጅት የቆመው ከእርሱ በፊት ትግራይ ውስጥ ተፈጥረው ይንቀሳቀሱ

የነበሩ እነ (ጠርናፊትን፣ ቲ.ኤል.ኤፍን) በተኹበት ጨፍጭፈው ነው እዚህ የደረሱት፤ ይህ የታሪካቸው አሻራ ነው። ከዚያ በኋላም ቢሆን ይህ አቶ አረጋዊ በርሄ ጋ ደርሶ ይዘዉት የነበረውን የድርጅት ሊቀ መንበርነት አቶ መለስ ሲነጥቋቸው፤ ሁለቱም በአደጉበት ተንኮልና ሴራ ሲተዳደኑ ቆይተው አቶ አረጋዊ በርሄ በመለስ ተበልጠው መለስ የበላይነቱን ሲይዙ፤ አቶ አረጋዊ የመለስ እስረኛ (የቁም እስረኛ) ሆነው እያሉ ከመለስ እሥር በዘዴ ወጥተው እንደቀሩ ከቆየው የታሪካቸው ማህደር እንብበናል። የዛሬ ጽሁፌ ዓላማ ኢትዮጵያን እያፈራረሱ ትግራይን ለማቆም የሚቃዡት የህወሓት/ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ. ሰዎች የሚያደርጉትን ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ ድርጊት እየተመለከትንና እየሰማን በአለንበት ሁኔታ አቶ አረጋዊ በርሄን የበላ ጅብ አልጮህ ማለቱ ቢደንቀኝ ነው። ለመሆኑ አቶ አረጋዊ በርሄ አሉ? የት ናቸው?

ህወሓት/ወያኔ ከ33 ዓመት በፊት ያለመውን ህልም ዛሬ በተመቸው ጊዜ ሥራ ላይ በማዋል ኢትዮጵያን ለሱዳን አሳልፎ በስጦታና በፈቃደኝነት እየሰጠ ነው። ይህ ድርጊት ቅድመ አያቶቻችን፣ አባቶቻችንና እናቶቻችን ከወራሪው ደርቡሽ ጋር ተጋድለው በደማቸውና በአጥንታቸው ድንበራችንን አስጠብቀውና እስካሁንም ድረስ ተከታዩ ትዉልድ እየተከላከለ አቆይቶ፣ አስጠብቆ የተረከብነውንና የተረከበውን ኢትዮጵያዊነትን ለምን ይሆን እነኝህ የህወኃት/ወያኔ ሰዎች ለማፈራረስ ይሄን ያህል ዘመን የደከሙትና የሚድክሙት? ለምን ይሆን ከቶ? ይህንን ጥያቄ የማቀርበው አቶ አረጋዊ በርሄንም ጨምሮ ለመላው የህወሓት/ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ መሥራቾች በሙሉ ነው። ይህ ቀደም ሲል ሲመሰረት ጀምሮ የቆመበት መሠረት፣ በስመ ጸረ አማራነት ሽፋን፣ በኢትዮጵያዊነት ላይ የተቃጣና የተሰነዘረ፣ የቆየ የህወሓት/ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ጥቃት፣ ኢትዮጵያን ውስጥ ውስጧን ሲያደማ፣ ሲያቆስል ቆይቶ ዛሬ በግልጽ በማናለብኝነት ለዋና ጠላታችን ለደርቡሽ መሬታችንን በጠራራ ፀሃይ እየሰጠ፣ ሕዝባችን በሱዳን(ደርቡሽ) እየተገደለ፣ ቤቱ እየተቃጠለ፣ ንብረቱ እየተዘረፈ በሚገኝበት ሁኔታ ላይ ምን ምክንያት ሊቀርብ ይሆን፣ አቶ አረጋዊ በርሄ ድምጻቸውን ለማሰማት ጊዜ የወሰደባቸው? በቅርቡ "ዓረና ትግራይ" በተባለው የእነ ገብሩ አሥራት ድርጅት ላይ የእነ መለስ ቡድን ወያኔ/ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ለአባላቱ ያወረደዉን ሰርኩላር አስመልክቶ ሰርኩላሩን በመቃወም የመጀመሪያ የተቃውሞ መግለጫ ለማውጣት የአቶ አረጋዊ በርሄ ድርጅት - "የትግራይ ዴሞክራሲያው ትብብር" (ታንድ) - ግንባር ቀደም ነበር። ታዲያ ከ"ዓረና ትግራይ" ድርጅት ኢትዮጵያ አንሳ ይሆን የታንድ መግለጫ የተነፈጋት? እንዴት እንዴት ነው ነገሩ ኀበዝ? (በቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ. ሰርኩላር በተላለፈበት የ"ዓረና ትግራይ" ድርጅት ላይ የአቶ አረጋዊ ታንድ(የትግራይ ዴሞክራሲያው ትብብር) ድርጅት በየካቲት 2 2008 ዓም ያወጣው መግለጫ በደቂ አሉላ ላይ ተለጥፎ ነበርና መመልከት ይቻላል።)

ለመሆኑ የወያኔ ሰዎች ከልጅነታቸው ጀምሮ ዕዉነት ይህንን ህልም ሲያልሙ ኢትዮጵያን አፍርሰው ትግራይ ትግርኝን፣ "ታላቋን ትግራይ" ለማቆም ነውን? ምን ዓይነት ቅዠት ነው! የቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ መሰራቾች ሆኑ ተከታዮች 70 ሚሊዮንን ኢትዮጵያዊ እየገደሉና እያሰሩ፣ ኢትዮጵያን እየወጉና እያደሙ፣ ህዝቧን በአጠቃላይ እየጠሉና ኢትዮጵያዊነትን ለመቅበር 33 ዓመት ሙሉ እየሰሩ እንዴት ኢትዮጵያዊ ናቸው ማለት ይቻላል? ሥራቸው በልፈፋ ብቻ ሳይገደብ በተግባር እየሰሩ የተጓዙበትን ሂደት ስንመለከተው፣ ዕውነት ኢትዮጵያዊ ናችሁ ብሎ ለሚጠይቃቸው መልሳቸው ምን ይሆን?
እነኝህ ሰዎች ይህን መሰል ድርጊት ሲፈጽሙ ራሳቸውን ከኢትዮጵያ ውጭ ቆጥረው ነውና ለመሆኑ ከየትኛው የውጭ ክፍል መጥተው ይሆን የወረሩን? በታሪካችን ኢትዮጵያን

*ለመውረር የመጡት ወራሪዎች (ጣሊያንና ደርቡሽ) የመጡበት የታወቀ፣ በዓለም የታሪክ መዝገብ ውስጥ የተቀመጠ፣ የውጭ ወራሪዎች መሆናቸው ግልጥ ነው። እነኝህን ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ-ኦችን አሁን ኢትዮጵያን ሀብቷንና ንብረቷን እየዘረፉ፣ ህዝቧንና ማንነቷን አናውቅም ያሉንን ወራሪዎች ከየት የመጡ እንበላቸው አቶ አረጋዊ በርሄ?*
*ከኢትዮጵያ የበቀሉ ብለን አፋችንን ሞልተን እንዳንናገር ኢትዮጵያን አይወዱ? ከውጭ የመጡ ናችው እንዳንል ወሰን አቋርጠው የመጡ የውጭ ወራሪዎች አልሆኑ? ታዲያ ኢትዮጵያዊው በሞላ እንደወራሪ ቆጥሮ ቢመለከታቸው "ወራሪዎች" አይደሉም ሊያስብላቸው የሚችል ባህሪያቸውን የሚያሳይ ተግባራቸው የትኛው ይሆን አቶ አረጋዊ? አይደሉምስ ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል? የትኛው ሚዛን ይሆን ወራሪው ጣልያን ካደረሰው ግፍ የሚያሳንሳቸው? ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ሥር የነበረች "ሌላ ሐገር" ናት ብሎ እወቁልኝ በማለት የዓለም መንግሥታትን አስጨንቆ የሞገተና በፈቃዱ ውሰዱልኝ ያለ የህወሓት/ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ፣ መንግሥት አይደለምን? ይህ (ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት) ናት የሚለው ሰነድ የአቶ አረጋዊ በርሄም አቋም የነበረ ነው። አቶ አረጋዊ ቀድሞ ከቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ጋር በነበሩበት ወቅት የተቀረጸው ይህ ኢትዮጵያን የሚቆራርጠው የህወሓት/ወያኔ ካርታ ከወጡም በኋላ የወልቃይት ጠገዴን ለም መሬትና ከወሎም የተወሰነ ክፍል ቆርሶ ወደ ትግራይ ክልል ሲያደርግ፣ አቶ አረጋዊ በርሄ ያወጡት/የሰጡት ይፋ መግለጫ ስለመኖሩ የማውቀው ነገር የለም። እርግጥ ነው አቶ አረጋዊ በርሄ ከቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ወጥተው የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር(ታንድ) የሚባል ድርጅት ማቋቋማቸው ይፋ ነው። ይህ የአቶ አረጋዊ ድርጅት ታንድ በኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ጉዳይ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ በተነጣጠር አደጋ ላይ ብዙ ጊዜ ግንባር ቀደም ሆኖ ድምጹን ሲያሰማ አልታየም፤ አልተሰማም፤ ለምን? በተለይ አሁን በግልጽ ከጎንደር እስከ ወለጋ ጫፍ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያ መሬታችንን ህወኃት/ወያኔ በድብቅ ለሱዳን በስጦታ ሲሰጥ አቶ አረጋዊ በርሄ የት ጠፉ? የወልቃየት ጠገዴ ለም መሬት ወደ ትግራይ ሲከለል ዝምታቸው ይገባኝ ይሆናል ግን ለትግራይ ተሰጥቶ ከትግራይ የተረፈው የኢትዮጵያ መሬታችን ለሱዳን ሲሰጥ፣ ብጣሽ ወረቀት ለማውጣት አለመቻሉ ለምን ይሆን? ከኢትዮጵያና ከአገር የበለጠሰ ምን የሚወጥር ነገር ተገኝቶ ነው? ኢትዮጵያ እየፈራረሰች ትግራይ ልትቆም? ደሮ ብታስብ ጥሬዋን!*

*ኢትዮጵያ በልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኖራለች!*
*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!*